## ትምህርት 3

**የኃጢአት ምንጩ ምንድነው?**

*ኃጢአት የሚፈጽመው ማንም ይሁን ማን፣ መነሻ ምንጩ/ምክንያቱ ግን ሶስት እንደሆኑ ከዚህ በታች የሰፈረው የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳል፡፡*

1. *ክፉ ምኞት የኃጢአት ምንጭ እንደሆነ ከሚናገሩት ጥቅሶች ለመጥቀስ ያህል፡-*

*ያዕ 1፡14-15፤ ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ክፉ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው። [15] ምኞትም ከፀነሰች በኋላ ኀጢአትን ትወልዳለች፤ ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።*

*ያዕ 4፡1፤ "በእናንተ መካከል ያለው ጦርነትና ጠብ ከየት የመጣ ነው? በውስጣችሁ ከሚዋጉት ምኞታችሁ አይደለምን?"*

*ኢያሱ 7፡20-21፣ አካንም መልሶ ኢያሱን፦ በእውነት የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን በድያለሁ እንዲህና እንዲህም አድርጌአለሁ። [21] በዘረፋ መካከል አንድ ያማረ የሰናዖር ካባ፥ ሁለት መቶም ሰቅል ብር፥ ሚዛኑም አምሳ ሰቅል የሆነ ወርቅ አይቼ ተመኘኋቸው፥ ወሰድኋቸውም፤ እነሆም፥ በድንኳኔ ውስጥ በመሬት ተሸሽገዋል፥ ብሩም ከሁሉ በታች ነው አለው።*

*ሚክያስ 2፡1-2 ክፉ ለመሥራት ለሚያቅዱ፣ በመኝታቸው ሳሉ ተንኰል ለሚያውጠነጥኑ ወዮላቸው! ሲነጋ በማለዳ ይፈጽሙታል፤ የሚያደርጉበት ኀይል በእጃቸው ነውና። [2] ዕርሻ ይመኛሉ፤ ይይዙታልም፤ ቤት ይመኛሉ፤ ይወስዱታልም፤ የሰውን ቤት፣ የባልንጀራን ርስት አታልለው ይወስዳሉ።*

*እነዚህ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች የሚያሳዩት ከልብ ከሚመነጭ ክፉ ምኞት የኃጢአት አንዱ መነሻ ምንጭ መሆኑን ነው፡፡*

*ቃኤልና አቤል የአንድ አባትና እናት ልጆች ሆነው በተመሳሳይ አካባቢና ሁኔታ አድገው ሳለ አቤል እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መስዋዕት አቅርቦ እግዚአብሔር ደስ ስለተሰኘበት ወንድሙ ቃኤል ክፉ አሳብ ስላሰበ (በወንድሙ ስለቀናና ስለተናደደ) አቤልን እንዴት እንደ ሚገድል ዕቅድ አውጥቶ ወደ መስክ ከወሰደው በኋላ በማጥቃት ገደለው፡፡*

2. *በመማር ኃጢአት እንደ ሚለማመድና እንደ ሚስፋፋ ከሚያሳዩ ብዙ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ጥቂቶቹ፡-*

*አንዱ ሰው ከሌላው ሰው ኃጢአት እንደሚማር/እንደ ሚለምድ ይታወቃል፡፡ ሰው ኃጢአት የሚማረው፣ የሚማረውን ነገር ሰምቶ ወይም ዓይቶ የራሱ ለማድረግ በልቡ ፈልጎት/ተመኝቶት ስለተቀበለው ነው እንጂ እንዲሁ በርሱ ላይ መጥቶ አይለጠፍበትም፡፡ ክፉ ነገርን መማርም ከፍላጎት/ከምኞት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ይህንኑ የሚያስረዱ ጥቅሶች፡ -*

*ዘፍጥረት 3፥6 "ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣ ለዓይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደሆነ ባየች ጊዜ፣ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ ሰጠችው፤ እርሱም በላ።" (አዳም ከሂዋን ኃጢአት ማድረግን ተማረ)፡፡*

*ዘዳ 18፥9፣ "አምላክህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) ወደሚሰጥህ ምድር በምትገባበት ጊዜ፣ በዚያ የሚኖሩት አሕዛብ የሚፈጽሙትን አስጸያፊ መንገድ አትማር/አትከተል::"*

ዘሌዋ 18:2-4 “ለእስራኤላውያን እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ ‘እኔ እግዚአብሔር (ያህዌ) አምላካችሁ (ኤሎሂም) ነኝ፤ [3] በኖራችሁበት በግብፅ እነርሱ እንደሚያደርጉት አታድርጉ፤ እኔ በማስገባችሁ በከነዓን እንደሚያደርጉትም አታድርጉ፤ ልማዳቸውንም አትከተሉ።

መዝ 106:34-37 እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት፣ ሕዝቦችን ከማጥፋት ወደ ኋላ አሉ፤ [35] እንዲያውም ከሕዝቦቹ ጋር ተደባለቁ፤ ልማዳቸውንም ቀሠሙ፤ [36] ጣዖቶቻቸውንም አመለኩ፤ ይህም ወጥመድ ሆነባቸው። [37] ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን ለአጋንንት ሠዉ።

ኤር 10፥2፣ “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “የአሕዛብን መንገድ አትከተሉ/አትማሩ/፤ እነርሱ በሰማይ ምልክቶች ይታወካሉ፣ እናንተ ግን በእነዚህ አትረበሹ።”

ምሳሌ 22:24-25፣ ከግልፍተኛ ጋር ወዳጅ አትሁን፤ በቀላሉ ቱግ ከሚልም ሰው ጋር አትወዳጅ፤ [25] አለበለዚያ መንገዱን ትማራለህ፤ ራስህም ትጠመድበታለህ።

1ኛ ቆሮ 15፥33 “አትሳቱ፤ “መጥፎ ጓደኝነት መልካሙን ጠባይ ያበላሻል።” (ኤር 2:24፣ 9:5፣ ሮሜ 6:12-13-16-19)

በተመሳሳይ ሁኔታ መልካም ተገባር መድረግም አንዱ ከሌላው የሚማረው ነገር ነው።

ኢሳ 1፥17 “መልካም ማድረግን ተማሩ፤ ፍትሕን እሹ፣ የተገፉትን አጽናኑ፤ አባት ለሌላቸው ቁሙላቸው፤ ለመበለቶችም ተሟገቱ።”

ኢሳ 54፥13፣ “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።”

ማቴ 11:29 ቀንበሬን ተሸከሙ፣ ከእኔም ተማሩ፣ እኔ በልቤ የዋህና ትሁት ነኝና ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ።

3. የሰይጣን (የክፉ መናፍስት) ማነሳሳት (መገፋፋት/ማሳት) ሌላው የኃጢአት መነሻና መማሪያ መንገድ ነው፡-

ዘፍ 3:1-6፣ በኤደን ገነት እግዚአብሔር ለአዳም አትብላ ካለው አንድ ዛፍ ፍሬ ሔዋን እንድትበላ ሰይጣን ገፋፋት። አዳምና ሔዋን የዚህ ዛፍ ፍሬ እዚያ እንዳለ ቢያውቁም ሳይበሉት ብዙ ቆይተው ነበር። በሰይጣን መገፋፋትና ዋሽቶ መልካም እንደ ሚሆንላቸው በመናገሩ ምክንያት ሰይጣንን አምነው ከፍሬው በሉ። የሔዋንና አዳም ኃጢአት ምንጩ ሰይጣን ነው። ክፉ መናፍስት በቀጥታ ራሳቸው ወይም ሰውን በመጠቀም ሌሎች ሰዎችን በማሳት በኃጢአት እንደሚዘፍቁ የተለያዩ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ያስረዳሉ። የአስቆሮቱ ይሁዳ ጌታ ኢየሱስን ለጠላቶቹ አሳልፎ የሰጠው ሰይጣን ከገባበት በኋላ ነው። ጌታ ኢየሱስ ዲያብሎስን ሐሰተኛ የሐሰትም አባት (ምንጭ) ነው ብሎታል። 1ነገ 22:19-22፣ 2ቆሮ 11:13-15፣ 2ተሰ 2:9-12፣ 1ጢሞ4:1-3፣ ራዕ 20:7-10፣ ይህንኑ ያሳያሉ።

**ስለዚህ ከላይ የሰፈሩት ጥቅሶች እንደሚያስረዱት፡-**

- ከእግዚአብሔር ባልሆነ ክፉ ምኞትና የሞኝነት ሃሳብ/ዕቅድ ኃጢአት ይጸነሳል፤ ክፉ ምኞት በተግባር ሲውል ኃጢአት ይወለዳል፤

ሰው ኃጢአት በማድረግ ጸንቶ/ወዶ ሲቀጥል የዘላለም ሞት ፍርድ ያስከትልበታል ማለት ነው፤

- ሰው ኃጢአት የሚያደርግበት ሁለተኛው ምክንያት አንዱ ከሌላው ኃጢአት በመማር ነው፤ ኃጢአት አንዱ ከሌላው በመማር ይስፋፋል/እየበዛ ይሄዳል፡፡
- ሰው በክፉ መናፍስት በመገፋፋት ኃጢአት ወደ ማድረግ ይገባል፡፡ ይህን ሲያደርግ ክፉ መንፈስ እየነዳው መሆኑን ላያውቀውና ከራሱ ኃሳብ የመነጨ ሊመስለው ይችላል፡፡ የሰይጣን ስራው ኃጢአት ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ኃጢአት የማድረግ ሃሳብ ወደ አእምሯችን ሲመጣ ክፉ መንፈስ እያነሳሳን እንደሆነ በመገንዘብ የእርሱን ግፊት አልቀበልም ማለት መቃወም ይገባል፡፡

**የኃጢአት አጀማመርና መስፋፋት፡** - ኢሳ 14፡9-20

**ዮሐንስ 8፥44** "እናንተ የአባታችሁ **የዲያብሎስ** ናችሁ፤ የአባታችሁንም ፍላጎት ለመፈጸም ትሻላችሁ። **እርሱ ከመጀመሪያ** ነፍሰ ገዳይ ነበር፤ በእርሱ ዘንድ እውነት ስለሌለ በእውነት አልጸናም፤ እርሱ ሐሰተኛ፣ የሐሰትም አባት በመሆኑ ሐሰትን ሲናገር፣ የሚናገረው ከራሱ አፍልቆ ነው፤"

**1ኛ ዮሐንስ 3፥8** "ኀጢአትን የሚያደርግ ከ**ዲያብሎስ** ነው። ምክንያቱም ዲያብሎስ **ከመጀመሪያ** አንሥቶ ኀጢአትን የሚያደርግ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠውም የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ ነው።"

በመጀመሪያ ኃጢአት ያደረገው ፍጥረት ሰይጣን ሲሆን፤ እርሱም ብዙዎች የእግዚአብሔር መላዕክትን በማሳት የራሱ መንገድ ተከታዮች እንዲሆኑ እንዳደረገ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል፡፡ ሰይጣን ከሚጠራባቸው ሌሎች ብዙ ስሞቹ መካከል ዲያብሎስና የቀደመው እባብ የሚባሉት ይገኙበታል፡፡

**ከሰው ዘር የመጀመሪያዎቹ ኃጢአተኞች ደግሞ አዳምና ሂዋን ሲሆኑ** እነርሱ ኃጢአት እንዲያደርጉ ዋሽቶ ያነሳሳው (የገፋፋው) ራሱ ሰይጣን እንደሆነ ዘፍ 3፡1-7 ያለው ክፍል ያስረዳል፡፡ ስለዚህ አዳምና ሂዋን የመጀመሪያዎቹ ኃጢአት ያደረጉ ሰዎች ናቸው፡፡ ኃጢአት ያደረጉበትም ምክንያት ያስገደዳቸው ማንም ሳይኖር እግዚአብሔር እንዳይበሉት ያዘዛቸው ፍሬ ለዓይናቸው ስላማራቸውና እንደ እግዚአብሔር መሆን ስላጓጓቸው (ስለ ፈለጉ) ነው፡፡

(ዘፍጥረት 3፡4-6፣ እባቡም ሴቲቱን እንዲህ አላት፤ "መሞት እንኳ አትሞቱም፤

[5] ከፍሬው በበላችሁ ጊዜ ዐይናችሁ እንደሚከፈትና መልካምና ክፉን በማወቅ፣ እንደ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) እንደምት ሆኑ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ስለሚያውቅ ነው።"

[6] ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣ **ለዐይን የሚያስደስትና** ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደሆነ ባየች ጊዜ፣ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ ሰጠችው፤ እርሱም በላ።)

ስለዚህ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እየተዋለደ የመጣው የሰው ዘር አንዱ ከሌላው ኃጢአት እየተማረና በራሱ የዓይን አምሮተና በልቡ ክፉ ምኞት (እንደ እግዚአብብሔር ፈቃድ ያልሆነ ምኞት) እየተሳበ ሁሉም በኃጢአት የተበከለ ሆነ፡፡